| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "ፀረ ፡ ዐማራነት ፡ ፀረ ፡ ሀገራዊነት ፡ ነው ። " |
| ደሆሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2013-005 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

## ፀረ ፡ ዐማራነት ፡ ፀረ ፡ ሀገራዊነት ፡ ነው ።



የካቲት ፡ 23 ፡ ቀን ፡ 1888 ፡ ዓ.ም. ፡ ዐድዋ ፡ ላይ ፡ ቅኝ ፡ ገዢነትን ፥ ሚያዝያ ፡ 27 ፡ ቀን ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. ፡ ደግሞ ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ ፋሺዝምን ፡ ድል ፡ አድርገናል ። ኹለቱም ፡ ድሎቻችን ፡ የሀገራዊነት ፡ ድሎች ፡ ናቸው ። ኹለቱ ፡ ጠላቶቻችንም ፥ ቅኝ ፡ ገዢነትና ፡ ፋሺዝም ፥ የምልክዮሽ ፡ (የ"ኢምፔሪያሊዝም") ፡ ክሥተቶች ፡ ናቸው ። ምልክዮሽ ፡ ግን ፡ ፀረ ፡ ሥልጣኔ ፡ ነጣቂ ፡ ኀይል ፡ ነውና ፥ በእየዘመኑ ፡ ምግባሩንና ፡ ስልቱን ፡ እያደሰ ፡ ይከሠታል ። በቀደመ ፡ ክሥተቱ ፡ ድል ፡ ቢደረግ ፥ በሌላ ፡ ዐዲስ ፡ ክሥተት ፡ ተመልሶ ፡ ከቸች ፡ ስለሚል ፥ ምልክዮሽ ፡ እያለ ፡ ሀገር ፡ ሰላም ፡ አታድርም ።

ሰራዊት ፡ እየላኩ ፡ ሀገርን ፡ መንጠቅ ፡ ዱሮ ፡ ቀረ ። ዛሬ ፥ የእጅ ፡ አዙር ፡ አገዛዝን ፡ በሀገር ፡ ላይ ፡ ተክሎ ፥ በከፋፍለኽ ፡ ግዛ ፡ ስልት ፥ በመንደር ፡ ገነኖች ፡ አማካይነት ፥ የተሻለ ፡ ውጤት ፡ ባነሰ ፡ ወጪ ፡ መገኘቱን ፡ ምልክዮሽ ፡ ስላረጋገጠ ፥ ይህኑ ፡ በሥራ ፡ አውሏል ። በቀጥታ ፡ ጦርነት ፡ ያልተሸነፈች ፡ ሀገር ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንደ ፡ ምሥጥ ፡ ሰርስሮ ፡ የሚያፈራርስለትን ፡ የኢ..ፌ.ዴ.ሪ.ን ፡ የአፓርትሀይድ ፡ ሥርዐት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ በዘዴ ፡ ተክሏል ። መመኘት ፡ አንድ ፡ ነገር ፥ መኾን ፡ ሌላ ፡ ... ፤ በ27ኛ ፡ ዓመቱ ፥ የኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ሕንጻ ፥ ያፈርሳታል ፡ ከተባለችው ፡ ሀገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ በፊት ፡ ራሱ ፡ ተሰነጣጥቆ ፡ ሊደረመስ ፡ ተቃረበ ፤ ከመደርመስም ፡ ሊያድነው ፡ የሚችል ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ምድራዊ ፡ ኀይል ፡ አልተገኘም ።

የኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፥ 27 ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ከቶ ፡ ምንን ፡ ሲያፈርስ ፡ ቈየ ፥ በተለይ ፡ ዒላማው ፡ ያደረገውስ ፡ ማንን ፡ ነበር ፥ "ሕገ ፡ ውንብድና"ው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ በመካድ ፡ "እኛ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝቦች ፣ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦች" ፡ በማለት ፡ ነገሩን ፡ ወጥኗል ፤ በሌላ ፡ አነጋገር ፥ "ሀገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ ባለቤት ፡ ሕዝብ ፡ የላት ፥ የግዛት ፡ አንድነትም ፡ የላት" ፡ ብሎ ፡ ሀገር ፡ የማፍረስ ፡ ምኞቱን ፡ ዐውጇል ። በዚሁ ፡ መሠረት ፦

- ባንድ ፡ ወገን ፡ "ኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ ሀገር ፡ ናት ፥ ባለቤቷም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በአንድነቱ ፡ ነው" ፡ ብሎ ፡ የሚያምነውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ ዐማራ ፥ ፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ እንዳደረገችው ፡ ኹሉ ፥ "ዐምሐራ/ነጻ ፡ ሕዝብ" ፡ የሚለውን ፡ የመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የግብር ፡ ስም ፡ ለተምሳሊታዊው ፡ "ክልል" ፡ በመስጠት ፥ "ቀፍድደነዋል ፣ ለይተነዋል ፣ አግልለነዋል ፣ አሳንሰነዋል" ፡ የሚል ፡ ክፉ ፡ ምኞቱን ፡ ገልጿል ፤
- በሌላ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፥ ለግንጠላ ፡ የሚዘጋጁ ፡ "ክልሎችን" ፡ በፀረ ፡ ሀገር ፡ ስብከት ፡ ኰትኵቶ ፡ በሀገራዊ ፡ ሕዝብናቸው ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በዐማራነታቸው ፡ ላይ ፡ እንዲያምፁና ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ደም ፡ እንዲቃቡ ፡ አድርጎ ፡ ሊለያያቸው ፡ ሞክሯል ።

ዐማራነት ፥ ክልል ፡ የማይከልለው ፣ ማንነት ፡ የማያጠበው ፡ ፍጹም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ሀገር ፡ ኢትዮጵያን ፡ አፈርሳለኹ ፡ ብሎ ፡ የሚመጣ ፡ የውጭ ፡ ኀይል ፡ ኹሉ ፥ ዐማራን ፡ አንድያ ፡ ዒላማው ፡ አድርጎ ፡ ያጠቃዋል ። ኾኖም ፡ ድል ፡ አድርጎት ፡ አያውቅም ፥ ወደ ፡ ፊትም ፡ ድል ፡ አያደርገውም ። ምክንያቱ ፡ አንድ ፡ ነው ፦ ሀገር ፡ የምትሠራው ፡ በርትዕ ፡ ሥልጣኔ ፡ መሠረትነት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በሥልጡንሕዝብናው ፡ ርትዕ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሠራ ፡ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሥልጡንሕዝብ ፥ ለርትዕ ፡ ሥልጣኔ ፡ ካል ኾነ ፡ በቀር ፡ ለሌላ ፡ ለምንም ፡ ዐይነት ፡ ኀይል ፡ አይሸነፍም ። ይህ ፡ ጽድቁ ፡ መለኮታዊ ፡ ጥበቃንም ፡ ሰጥቶታልና ፥ በጕልበት ፡ እናሸንፈዋለን ፡ እያሉ ፡ በግፍ ፡ የመጡበት ፡ ነጣቂዎች ፡ ኹሉ ፥ በቅርብ ፡ ታሪክ ፡ ብቻ ፥ ለኹለት ፡ የዓለም ፡ ጦርነቶች ፡ ተዳርገው ፡ ተቀጥተውለት ፡ ነበር ፤ ዛሬም ፥ አያድርግባቸውና ፥ ለሌላ ፡ ዙር ፡ ዕልቂት ፡ የተደገሱ ፡ ይመስላል ፡ ❖

እግዚአናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ..ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!

ኢ.ሀ.ሥ.አ.

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።